# አባ ለየላቸው

ገዳሙን አቃጥለው በስውር መርዛቸው
ባህታዊውን ገለው በጥልቅ መርፌያቸው
ቄስና ዲያቆኑን ከመቅደስ አግደው
ሊቃውንት አልባ ማህሌት መርግደው
አባ ለየላቸው በክህነቱ ገቢ ቀሩ በርቃናቸው፡፡

አባ በስም እንጂ ቆየ ማበዳቸው
መስቀልና ሽጉጥ ተቀላቅሎባቸው
የመለስ ካድሬ ግንባር ቀደም ናቸው
አባ ለየላቸው ጳጳሱን በዱላ በሽጉጥ ሸኟቸው፡፡

ቀድሞውንም ቢሆን አጠለቁት እንጂ
ካባና ቆቡን
አነገቡት እንጂ ዳዊት መስቀሉን
እጃቸው ክላሽ ነው ልባቸው መለስን
ፍፁም አብዮታዊ ዲሞክራሲውን
አባ ለየላቸው ፈጁት ካህኑን፡፡

የተባረክንበት ረቂቁን የአምላክን ስጦታ
በሮም አደባባይ ለግብረ ሰዶሞች በፀያፉ ቦታ
በቡናችን ምትክ ሊያሻግሩት ኬላ
አምላክ አያይ ብለው በአግኣዚ ጥበቃ
በአግኣዚ ከለላ
አባ ለየላቸው በፅላተ ሙሴ በሉበት ድላላ

ትግራይ እሪ በይ ቀደምት ክርስቲያን
አክሱም ተናገሪ ደብረ ቅዱሳን
አባ ሳይሰውሩት ፅላተ ሙሴን፡፡

አድዋም በልጆችሽ ይቅር መለሳለስ
ተነቤንና ማይጨው ይብቃችሁ መታገስ
አባን አንድ በሉን ይበቃል የመለስ
ሁሉንም ለማርከስ፡፡

በቀይ ሽብር አዋጅ አባረው መለኩሴ
አባ ለየላቸው በወታደር ፖሊስ አወጁ ቅዳሴ፡፡

## ከሁለት ያጣ አይሁን

ንሥሃ እንዳይገባ ለማን ይናዘዘው
አባው መስቀል ጥሎ የጦር ካፒቴን ነው
ዓለማዊ እንዳይሆን ምድሩን መለስ ቀማው
ህዝብ ግራገብቶት የመጨረሻዋን ቀን ትንቢት
ጠባቂ ነው፡፡

በዋልድባ ገዳም በቁልቢው ገብርኤል
በአሰቦት ዝቋላ እንዲሁም ዜጋመል
በአርምሞ ያላችሁ እነ አባ ሣሙኤል፡፡
ለእናንተ አይሰወር የአምላክ ሚስጢር ቃሉ
ዝምታው ይብቃና እስቲ አንድ በሉ፡፡

ንገሩት የትንቢት ፍፃሜው ጊዜው መቃረቡን
አባት በልጆቹ ሽጉጥ መተኮሱን፡፡

የንስሃው ቦታ የሱባኤው መግቢያ
የመናኞች ሠፈር የፃድቃን ማረፊያ
የምእመናን ጥላ አምላክን ማምለኪያ
ዋልድባ መንደዱን አሰቦት መብገኑን
ዝቋላ ሲቃጠል ዐይናችሁ ማየቱን፡፡

ይወቀው ትንቢቱን ሁሉም መፈፀሙን
አገር ለእጅ መንሻ ተቆርሳ መሄዷን
ገጠሬው መሬቱን በአረብ መወረሱን
እህል ከአገር ጠፍቶ ሰውን ሰው መበላቱን
ከተሜው በጨለማ በውሓ ጥም ማለቁን፡፡

ለአውደ አመትባሉ  ያስለመደው ቀርቶ
አጥንት መዋዋሱን ማጣፈጫ አጥቶ፡፡
ደግማችሁ ንገሩት የምድሩ ማብቃቱን
ከሁለት ያጣ አይሁን ያጠንክር እምነቱን፡፡
መኖር እንደውአይችል ሚዛን ውሉን ስቷል
ሽያጭ ግብይቱ ሁሉም በሺ አልቋል፡፡

ዳግምዓለም

ነሐሴ:2001